## የሞንጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ

## በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የጤና ክፍሎች ሌይቴክስ ኮንዶም እና የትምህርት ፕሮግራም ስለሚገኝ

### በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች

**ጥ1** ለምንድነው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች (DHHS) ኮንዶሞችን እና በወሲብ ግንኙነት ተላላፊ ጥቃቶችን (STI) የመከላከል ትምህርት ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤ ተማሪዎች እንዲሰጥ የሚያደርጉት?

**መ1** በወሲብ ግንኙነት ተላላፊ ጥቃቶች (STIs) በሞንትጎመሪ ካውንቲ በተለይም ከ15 - 19 አመት እድሜ ክልል ውስጥ ባሉ ነዋሪዎች በከፍተኛ ደረጃ/በአስጊ ሁኔታ እየጨመረ በመሄዱ ምላሽ ለመስጠት ከጤና እና ሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ -DHHS ኮንዶሞችንና በወሲብ ግንኙነት ተላላፊ ጥቃቶችን (STI) የመከላከል ትምህርት ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች እንዲያገኙ መደረግ እንዳለበት ሀሳብ ቀርቧል። ከጤና እና የማህበራዊ አገልግሎት መምሪያ ጋር በመተባበር አጠቃላይ የጤና ትምህርትን/ከሪኩለም ለማጠናከር እና ሌቴክስ ኮንዶሞችን እና በወሲብ ግንኙነት ተላላፊ ጥቃቶችን (STI) የመከላከል ትምህርት ፕሮግራም ከኦክቶበር 1/2018 ጀምሮ በሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የጤና ክፍሎች የማቅረብ ስምምነት እንዲዳብር የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ሴፕቴምበር 11/2018 ወስኗል።

ይህ ፕሮግራም ለተማሪዎች ሪሶርስና ድጋፍ የማቅረብ እና ምርጫቸው ጤናማ እና በእውቀት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS ) ካለው ሰፊ ስትራተጂ ጋር ይጣጣማል። ሌሎች ይህንን ስልት/ስትራቴጂ የሚያጠናክሩ ፕሮግራሞች በየአመቱ የሚካሄደው "መከባበርን ምረጥ/ምረጪ ሞንትጎመሪ ኮንፈረንስ/Choose Respect Montgomery conference" የተሰኘው ወጣቶች በፍቅር ግንኙነት መከባበርን እና በአፍላ ልጅነት አብረው በሚያሳልፉበት የፍቅር ጊዜ ጠብ/ረብሻ ሊያደርጉት የሚገባ ጥንቃቄ የግንዛቤ ማሳደጊያ፣ እና አጠቃላይ የጤና ትምህርት ከሪኩለም ትኩረት የሚያደርግባቸዉ፣ የግብ-አቀማመጥ የህይወት ተሞክሮዎችን፤ ስለ ውሳኔ አሰጣጥ፤ እምነቶችን፣ አመለካከቶችን፣ እና ተነሳሽነቶችን መለየት፤ መረጃዎችን/ኢንፎርሜሽን ማገናዘብ፤ እና ስለ ግል፣ የቤተሰብ፣ እና የማህበረሰብ ጤና ተሚጋች መሆንን ያካትታል።

**ጥ2** የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ኮንዶም ለመጠየቅ የሚችሉት እንዴት ነው?

**መ2** የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ ከት/ቤት ማህበረሰብ የጤና ነርስ (SCHN) ጋር ለመነጋገር ይጠይቃል/ትጠይቃለች። በወሲብ ግንኙነት የሚተላለፉ ጥቃቶች (STI) ትምህርት የሚታሰበዉ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የመራቢያ ጤንነት ካውንስሊንግ ሂደት የሚያካትተዉን በወሲብ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን (STIs) ለመከላከል ሌቴክስ ኮንዶሞችን መጠቀም እንደሚያስፈልግ የሚሰጥ የጤና ትምህርት አካል ተደርጎ ነው።

**ጥ3** **ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የጤና ክፍል ስንት ኮንዶሞች ናቸው የሚሰራጩት?**

**መ3** ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የጤና ክፍል በየወሩ ኮንዶሞችን የሚያሠራጨው የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ (DHHS) ነው። አብዛኛዎቹ ት/ቤቶች እያንዳንዳቸው አምስት ኮንዶሞች ያሉበት ቢያንስ 20 ትናንሽ ቡኒ/ቡናማ ቀለም የወረቀት ከረጢቶችን ያገኛሉ። በመደበኛነት ለተማሪዎች እና ለቤተሰቦቻቸው (በወሲብ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች ምርመራ ጨምሮ) የህክምና እንክብካቤ የሚሰጡ Wellness Centers-ጤናማ/ጥሩ አቋም ላይ የመሆን ማእከሎች ያሏቸው አራት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች እያንዳንዳቸው አምስት ኮንዶሞች ያሉበት ቢያንስ 40 ከረጢቶችን ያገኛሉ።

**ጥ4** **ለሚጠይቁ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ስንት ኮንዶሞች ይሰጣቸዋል?**

**መ4** የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በአንድ ጊዜ ጉብኝት አምስት ሌቴክስ ኮንዶሞችን የያዘ አንድ ከረጢት ያገኛሉ።

**ጥ5** **የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ከት/ቤት ማህበረሰብ ነርሶች ጋር ለመነጋገር በሚጠይቁበት ጊዜ ነርሶቹ መከተል ያለባቸው ፕሮቶኮል/ሥርዓት ምንድነው?**

**A5** የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ ያዘጋጃቸው ማስተማሪያ ቁሳቁሶች ስላሉ የት/ቤት ማህበረሰብ ነርሶች እርሱን ተከትለው እንዲሠሩ ሥልጠና ተሰጥቷቸዋል። የማስተማሪያ ነጥቦቹ የሚያካትቱት፦

- በወሲብ ግንኙነት የሚተላለፉ ጥቃቶችን (STIs) የሌቴክስ ኮንዶሞችን በመጠቀም እንዴት ለመከላከል እንደሚቻል
    - የወንድ ሌቴክስ ኮንዶምን በመደበኛነት በትክክል መጠቀም በወሲብ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን (STI) እና የኤች. አይ. ቪ ኤድስ/human immunodeficiency virus (HIV) የመተላለፍ ስጋት ይቀንሳል።
    - ኮንዶምን መጠቀም በወሲባዊ ግንኙነት የሚተላለፉ ጥቃቶችን (STI) ለመከላከል ፍጹማዊ መፍትሔ አይሆንም። በወሲባዊ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን (STIs) ለመከላከል በጣም አስተማማኙ መንገድ ከወሲባዊ ግንኙነት መቆጠብ፣ ወይም በበሽታ ያልተለከፈ/ች ሰው ጋር አንድ ለአንድ ግንኙነት ብቻ ለረዥም ጊዜ መቆየት ነው።
    - ኮንዶሞችን በመጠቀም ከፍተኛውን ጥበቃ/መከላከል ለማግኘት የሚቻለው፣ በቋሚነት እና በትክክል በመገልገል ነው።
    - የኮንዶሞች አጠቃቀም በወሲባዊ ግንኙነት የሚተላለፉ ጥቃቶችን እና ኤች.አይ.ቪ ኤድስን (STI/HIV) ለመከላከል ያለመቻል የሚፈጠረው ከኮንዶሙ ሳይሆን በአብዛኛው በመደበኛነት ካለመጠቀም ወይም ከትክክለኛ የአጠቃቀም ጉድለት ነው።
    - በመደበኛነት ያለመጠቀም ወይም በፍጹም አለመጠቀም በወሲባዊ ግንኙነት በሚተላለፉ በሽታዎች (STI) ወደ መጠቃት/መለከፍ ሊያመራ የሚችል ሲሆን በሽታው ከያዘው/ከያዛት ሰው ጋር የአንድ ጊዜ የወሲብ ግንኙነት በመፈጸም ምክንያት በበሽታው መለከፍ ሊከሰት ይችላል።
- ኮንዶምን በመደበኛነት እና በትክክል እንዴት ለመጠቀም እንደሚቻል

- ○ በእያንዳንዱ ወሲባዊ ግንኙነት ወቅት በማናቸውም ዓይነት የግብረስጋ ግንኙነት (የሴት ብልት፣ በፊንጢጣ፣ እና የአፍ) ሲደረግ ከምንም የወሲብ ድርጊት (የአባለዘር/ሀፍረተ ስጋ) ንኪኪ አስቀድሞ ከመጀመሪያ እስከ ፍፃሜው አዲስ ኮንዶም መጠቀም ያስፈልጋል።
  - ○ የኮንዶም ትክክለኛ አጠቃቀም ሂደት/ቅደምተከተል (ጊዜው ያለፈበት አለመሆኑን ጭምር እና ኮንዶሙ የብልሽት ምልክት እንደሌለው ማረጋገጥ)።
  - ○ በወሲባዊ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመከላከል የኮንዶምን ውጤታማነት ሊቀንስ የሚችለው ምንድን ነው (STIs) (ለምሳሌ፡- ማለስለሻ-ዘይት/ቅባት መጠቀም)።
- የኮንዶም ማከማቻ
  - ○ በቀጥተኛ የፀሐይ ብርሃን ወይም ፍሎሮሰንት (አምፑል) ብርሃን የተጋለጠ፣ ሙቀት፣ እርጥበት አዘል አየር፣ እና የኦዞን ንብርብር የኮንዶምን ክምችት መደርደሪያ ላይ የመቆየት እድሜ በጣም ሊያሳጥር ይችላል።
  - ○ ኮንዶም ከመጠቀምዎ በፊት አገልግሎቱ የሚያበቃበትን ጊዜ ፓኬጁ/ካርቶኑ ላይ ይፈትሹ። የኮንዶም መያዣው ምንም ያልሆነ/ያልተጎዳ፣ ያልተጣበቀ፣ የማያዥ/ፍሳሽ የሌለው መሆን አለበት።
  - ○ የኮንዶም መያዣዎች ያልተጨማደዱ፣ ወይም ለብልሽት ያልተጋለጡ መሆን አለባቸው።

የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ሌሎች ሁለት መገልገያዎች/ሪሶርስ ሠነዶች ጭምር ይሰጣቸዋል፡-

- https://www.cdc.gov/condomeffectiveness/docs/condomfactsheetinbrief.pdf.
- https://www.cdc.gov/condomeffectiveness/male-condom-use.html (በተለያዩ ቋንቋዎች ይገኛል)።

**ጥ6** እነዚህ የጤና ክፍል ጉብኝቶች ሪኮርድ ይደረጋሉ? ከሆነስ፣ እንዴት?

**መ6** አዎ፣ ወደ ጤና ክፍል የሚደረጉ ሁሉም ጉብኝቶች በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የተማሪዎች የጤና ፋይል ላይ ሪኮርድ ይደረጋሉ። የት/ቤት ማህበረሰብ የጤና ነርስ ካለ/ች ጉብኝቱ "ከማህበረሰብ የጤና ነርስ ጋር የተደረገ ኮንፈረንስ/Conference with SCHN" ተብሎ ሪኮርድ ይደረጋል። የት/ቤት ማህበረሰብ የጤና ነርስ ከሌለ/ች፣ SHRT "የት/ቤት ማህበረሰብ የጤና ነርስ ለማየት ጥያቄ/Request to see SCHN." በማለት ይመዘግባል/ትመዘግባለች። የት/ቤት ማህበረሰብ የጤና ነርስ ስንት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ኮንዶሞችን እንዳገኙ እና ስለአጠቃቀሙ፣ እና በወሲባዊ ግንኙነት ስለሚተላለፉ ጥቃቶችን (STIs) ስለመከላከል ትምህርት እንደተሰጣቸው ቁጥሩን ይመዘግባል/ትመዘግባለች።

**ጥ7** ለልጆቻቸው ኮንዶም እንዳይሰጣቸው ወይም በወሲብ ግንኙነት ስለሚተላለፉ ተዛማጅ በሽታዎች (STI) ትምህርት እንዳይሰጣቸው ወላጆች/ሞግዚቶች ለመጠየቅ ይችላሉ?

**መ7** የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ኮንዶም እና በወሲብ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን (STI) የመከላከል ትምህርት ከጠየቁ፣ ወላጆች/ሞግዚቶች የእነርሱ ተማሪ ኮንዶም ወይም ተዛማጅነት ያለው

በወሲብ ግንኙነት የሚተላለፉ ጥቃቶችን (STI) የመከላከል ትምህርት እንዳይሰጣቸው አይጠይቁም። [1]

**ቁ8** ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ የሆነ/ች የእኔ ልጅ ለሌቴክስ አለርጂ ከሆነ/ች ምን ይደረጋል?

**መ8** ሌቴክስ አለርጂ የሚሆንበት/የሚሆንባት ማንኛውም ተማሪ በትምህርት ቤት ማህበረሰብ የጤና ነርስ አማካይነት ለዚህ ጥቅም ያላቸው ሌሎች አማራጮች መኖራቸውን እና ስለ አቅርቦቱ ካውንስል ይደረጋል/ካውንስል ትደረጋለች።

**ጥ9** የጤና ክፍሉ የትኞቹ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ኮንዶሞችን እንዳገኙ ዝርዝር/ሊስት ይኖረዋል?

**መ9** የጤና ክፍሎቹ ኮንዶሞች እና በወሲባዊ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን (STI) የመከላከል ትምህርት የተሰጣቸው ተማሪዎች ቁጥር ይኖረዋል። የተማሪዎቹ ይፋ መጠሪያ ስም ዝርዝር ተይዞ አይቆይም።

**ጥ10** "በወሲብ ግንኙነት የሚዛመቱ በሽታዎች" "STDs" በማለት ፈንታ "በሚዛመት የግብረስጋ ግንኙነት ጥቃት/መለከፍ" "STIs" የሚሉትን ቃላት የምትጠቀሙት ለምንድነው?

**መ10** ቃሎቹ በመተካካት የሚጠቀሙ ቢሆንም የተለያየ ትርጉም አላቸው። "በሚዛመት የግብረስጋ ግንኙነት ጥቃት/መለከፍ" ማለት ሰፊ ትርጉም ሲሆን በእርግጥ ግለሰቡ/ቧ የተያዘ(ች)/የተለከፈ(ች) ቢሆንም ገና በሽታ በሚሆን ደረጃ እንዳላደገ ያመለክታል። መጠቃት/መለከፍ ወደ በሽታ የሚያመራ የመጀመሪያው ደረጃ ሲሆን ከማንኛውም ዓይነት ወደ ሰውነት ውስጥ ከገባ በኋላ ከሚራባ የባክቴሪያ/ረቂቅ ህዋስ፣ የቫይረስ/ተላላፊ በሽታዎችን አምጪ ረቂቅ ህዋስ፣ ወይም የሚክሮብ/በሽታ አምጪ ረቂቅ ነፍሳት/ተሃዋሲ ውጤት ሊሆን ይችላል። በወሲብ የሚዛመት መጠቃት/መለከፍ (STI) ያለበ(ባ)ት ሰው የበሽታ ወይም የህመም ምልክት ላይታይበ(ባ)ት ይችላል ቢሆንም ግን ተሸካሚ እና ለሌሎች ጥቃቱን ለማስተላለፍ ይችላል/ትችላለች። አንድ/አንዷት ግለሰብ የሚዛመት የወሲብ ተጠቂ ሆኖ/ሆና በሽታው ላይጎለብትበ(ባ)ትም ይችላል። በመጨረሻ፣ በወሲብ የሚዛመት ጥቃት (STI) አብዛኛውን ጊዜ በወሲብ ከሚተላለፍ በሽታ (STD) ያነሰ መጠቋቆም/ማግለል ይኖረዋል።[2]

**ጥ11** የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ ኮንዶሞችን እና በወሲብ የሚተላለፍ ጥቃት/መለከፍ (STI) መከላከያ ትምህርት ሲጠይቅ/ስትጠይቅ ለወላጆች/ሞግዚቶች ይገለጽላቸዋል?

**መ11** አይገለጽላቸውም። የሜሪላንድ ደንቦች ህግጋት/Code of Maryland Regulations፣ ስለ ጤና አንቀጽ፣ ክፍል 20-102 እንደሚከተለው ይገልጻል "ትንሽ ወጣት ልጅ/ማይነር ስለ አባለ ዘር በሽታ፣ ህክምና ወይም ምክር ለመጠየቅ፣ ስለ እርግዝና ህክምና ወይም ምክር፣ ከማኮላሸት በስተቀር ስለ እርግዝና መቆጣጠሪያ ህክምና ወይም ምክር ለመጠየቅ እንደትልቅ ሰው አንድ ዓይነት ችሎታ አለው/አላት ይላል[3]

---

[1] http://mgaleg.maryland.gov/webmga/frmStatutesText.aspx?article=ghg&section=20-102&ext=html&session=2017RS&tab=subject5

[2] American Sexual Health (http://www.ashasexualhealth.org/).

[3] http://mgaleg.maryland.gov/webmga/frmStatutesText.aspx?article=ghg&section=20-102&ext=html&session=2017RS&tab=subject5

**ጥ12** የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ ወደ ጤና ክፍል ተመልሶ/ተመልሳ ተጨማሪ ኮንዶሞችን ለመጠየቅ አግባቡ እንዴት ነው?/ምንድነው መደረግ ያለበት?

**መ12** የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ እና የት/ቤት ማህበረሰብ የጤና ነርስ ስለኮንዶም ትክክለኛ አጠቃቀም እና በወሲብ ስለሚዛመት ጥቃት (STIs) መከላከያ ትምህርት አንድ ዓይነት/ተመሣሣይ ፕሮቶኮል መሙላት አለባቸው።

**ጥ13** የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ በወሲብ የሚዛመት ጥቃት (STIs) ለመከላከል ኮንዶሞችን ለማግኘት የጠየቀ/ች እንደሆነ የት/ቤት ሠራተኞች ማድረግ ያለባቸው ምንድነው?

**መ13** የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በወሲብ የሚዛመት ጥቃት (STIs) ለመከላከል ኮንዶሞችን ለማግኘት የጠየቁ እንደሆነ የት/ቤት ማህበረሰብ የጤና ነርስን እንዲያነጋግሩ ወደ ጤና ክፍል እንዲሄዱ ይደረጋል።

**ጥ14** ኮንዶም መስጠትና የትምህርት ፕሮግራም አጠቃላይ የጤና ትምህርት ካሪኩለምን እንዴት ነው የሚደግፉት?

**A14** በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ ከተመሠረቱት ከሰባት የጤና ትምህርት ይዘቶች ሁለቱ ይህንን ኮንዶም ለማግኘት እንዳያስቸግር ማድረግና የትምህርት ፕሮግራምን ያሟላሉ።

- ቤተሰባዊ ህይወት እና ሰብአዊ ወሲባዊነት
- የበሽታ መከላከል እና ቁጥጥር

በ 7ኛ፣ 8ኛ፣ እና 10ኛ ክፍሎች የጤና ትምህርት የሚያካትቱ ክፍሎች ከተላላፊ በሽታዎች እና በወሲብ የሚዛመቱ ጥቃቶችን (STIs) መከላከል እና ህክምና ጋር የሚገናኙ ናቸው። የ 10ኛ ክፍል አጠቃላይ የጤና ትምህርት ከሪኩለም የተለመዱ በወሲብ የሚዛመቱ ጥቃቶችንና (STIs) እንዴት እንደሚዛመቱ የሚገመግም እና ስለ በሽታዎች መከላከል እና ቁጥጥርን ያካትታል። አንድ አመላካች የሆነዉ "የኮንዶሞች በትክክለኛ እና በመደበኛነት አጠቃቀም የኤች.አይ.ቪ (HIV) እና ሌሎች በወሲብ የሚዛመቱ ጥቃቶች (STIs)፣ HPV ጭምር ያለውን ስጋት የመቀነስ ውጤታማነት ነው"።[4]

ከሪኩለሙ ላይ የተተኮረው የሚያሳድረውን ተጽእኖ በትንታኔ የማየት ችሎታ፣ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ማግኘት፣ ውሣኔ መስጠት፣ ራስን-መምራት፣ እና ተማሪዎች መረጃ/ኢንፎርሜሽን አግኝተው በእውቀት ላይ ተመስርተው መወሰን እንዲችሉ ማቀንቀን ላይ ነው። እነዚህ በኮሌጅ እና ስራ ላይ ጠቃሚ የሆኑ ክሂሎቶች ናቸው።

**ጥ15** በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች በሚገኙ የጤና ማእከሎች ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ኮንዶሞች ይሰጣቸዋል?

**መ15** በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት የሚገኙ የጤና ማእከሎች የሚያገለግሉት ትናንሽ ልጆችን እና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እድሜ ያሉትንም ተማሪዎች ጨምሮ ነው። ስለ መዋለድ ጤና እና በወሲብ የሚተላለፉ ጥቃቶችን (STI) ስለመከላከል ለመነጋገር/ለመወያየት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በትምህርት ቤት

[4] https://www.montgomeryschoolsmd.org/uploadedFiles/curriculum/health/high/grade10/Grade%2010%20Comprehensive%20Health%20Education%20Indicators%20and%20Objectives(1).pdf

የሚገኝ የጤና ማእከል ሲጎበኙ ኮንዶሞችን እና በወሲብ የሚዛመቱ ጥቃቶችን (STI) ስለ መከላከል ትክክለኛ አጠቃቀም ትምህርት ሊሰጣቸው ይችላል።

**ጥ16** የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎችን ጨምሮ ሰፊ የእድሜ እና የክፍል ልዩነት ያላቸውን ተማሪዎች በሚያገለግሉ ት/ቤቶች ወይም ፕሮግራሞችስ እንዴት/ምን ይሆናል?

**መ16** ሮክ ተሬስ ት/ቤት (Rock Terrace School)፣ የልጆች እና የጎልማሶች ክልላዊ ተቋም/Regional Institute for Children and Adolescents፣ እና የብሌር ጂ. ኢዊንግ የሁለተኛ ደረጃ ተ/ቤት ተማሪዎችን የሚያገለግል ማእከል /Blair G. Ewing Center serve high school students የት/ቤት ማህበረሰብ ጤና ነርስ ኮንዶሞችን ለሚጠይቅ/ለምትጠይቅ ማንኛውም ተማሪ የሚማርበትን/የምትማርበትን ክፍል ያጣራል/ታጣራለች። በእነዚህ ፕሮግራሞች የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች (ማለትም፦ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የሚገኙ ተማሪዎች) ኮንዶሞችን ሊያገኙ እና በወሲብ ተላላፊ የሆኑ ጥቃቶችን (STIs) ለመከላከል እንዴት መጠቀም እንደሚኖርባቸው ትምህርት ሊሰጣቸው ይችላል።